# «...ከጥቂቶቹ በስተቀር አብዛኛዎቹ የሃይማኖት መሪዎች የተከሰተውን ችግር በመቋቋም ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል» ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ

ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የሶማሊያ እስላማዊ ፍርድ ቤቶች ኅብረት የጂሃዲስቶች አመራር በኢትዮጵያ ላይ ያወጀውን የጅሃድ ጦርነትና ግልፅና ወቅታዊ አደጋ አስመልክተው፤ ከተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ በትናንትናው ዕትም ማቅረባችን ይታወቃል።

በሀገራችን በጅማ እና ኢሉ አባቦራ ዞኖችም በሃይማኖት ሽፋን ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሰላም ተልዕኮአቸውን ለማስፈጸም ከፍተኛ እንቅስቃሴ ባደረጉ አክራሪ ኃይላት ላይ መንግሥት የወሰደውን እርምጃና ሕዝብ የማረጋጋት ተግባር አስመልክተው፣ ለምክር ቤቱ አባላት የሰጡት ምላሽ እንደሚከተለው ቀርቧል።

በምዕራቡ የሀገራችን ክፍል በተለይም በጅማ እና በኢሉ አባቦራ ዞኖች ግጭት ከተፈ ጠረ በኋላ ክልሉ በራሱ ከወሰደው እርምጃ በተጨማሪ የፌዴራል መንግሥት ህግ አስከባሪ ኃይሎችም ወደ ቦታው ተልከው ከክልሉ ህግ አስከባሪ ኃይሎች ጋር በመተባበር ጉዳዩን ለማጣራትና ለማረጋጋት የተለያዩ እርምጃዎች ወስደዋል።

በዚሁ ሂደት ለማረጋገጥ የተቻለው በሁለቱም ዞኖች የደመራ በዓልን መሠረት በማድረግ የተፈጠሩ ግጭቶች እንደነበሩ ነው። ግጭቱ የተጀመረው መስከረም 16 ላይ ነው፤ በጅማ ዞን በሁለት ቦታዎች ሃኖ በሚባል አካባቢና የቡ በሚባል አካባቢ አንዳንድ ጽንፈኛ ኃይሎች የደመራ በዓል እንዳይከበር፣ ደመራ እንዳይተከልና እንዳይቀጣጠል ለማድረግ ጥረት አድርገው ነበር፤ የማስፈራራት ሥራም ሰርተው ነበር። በተለይ የቡ በሚባለው አካባቢ ደመራው እንዳይተከልና እንዳይቃጠል ለመከላከል ሞክረው ሳይሳካላቸው ከቀረ በኋላም ድንጋይ በመወርወር ችግር ለመፍጠር ሞክረው ነበር። ነገር ግን በእነዚህ በሁለቱ ቦታዎች በሃኖ እና በየቡ መስከረም 16 የተደረገው ሙከራ ሳይሳካ ቀርቶ የደመራ በዓል በታቀደለት መልኩ ተፈጽሟል።

ከዛ በኋላ በኢሉ አባቦራ ዞን የተፈጠረውን ችግር ተከትሎ በጅማም ዞን የተለያዩ ችግሮች ተከስተዋል። ነገር ግን መስከረም 16 ላይ የተሞከረውን ሙከራ ለማክሸፍ ተችሏል። በኢሉ አባቦራ ዞን ውስጥ ጨሎ በሚባለው አካባቢ የሚቀጣጠለው ደመራ በወትሮው ቦታ ሳይሆን በአካባቢው ወደ ነበረው መስጊድ ጠጋ ብሎ እንዲተከል ነበር የተደረገው። በመስጊዱ ይጠቀሙ የነበሩ ሙስሊም አማኞች ሰዓቱ የሶላት ስግደት የምንሰግድበት ሰዓት ስለሆነ ከሥራችንም ከሃይማኖታችንም ጋር ይጋጫል፤ በወትሮው ቦታ ተክላችሁ ብታቀጣጥሉ ይሻላል የሚል አስተያየት አቅርበዋል። በዚህ ጉዳይ ላይ በሁለቱም ሃይማኖት ተከታዮች አካባቢ የተለያየ ክርክር በመነሳቱ የሃይማኖት አባቶች ተገናኝተው ጉዳዩን በውይይት ለመፍታት በድርድር ላይ እያሉና ጉዳዩን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሃይማኖት አባቶች፣ የአገር ሽማግሌዎች እየተደራደሩ ባሉበት ወቅት በጐን አንድ የአካባቢው ቄስ አንድ የ14 ዓመት ታዳጊ ልጁን ልኮ ደመራውን ለማቀጣጠል ሞከረ።

ደመራውን ለማቀጣጠል በሞከረበት ወቅት በአካባቢው ይታዘቡ ከነበሩ ሙስሊሞች

ድንጋይ መወርወር ተጀመረ። ድንጋይ ከተወ ረወረ በኋላ አንድ በወቅቱ መጠጥ ወስዶ የመጣ ይሆናል ተብሎ የሚጠረጠር ልጅ መሣሪያ አውጥቶ ተኩስ በመክፈት አራት ሙስሊሞችን ገድሎ ስድስት አቆሰለ። ይህ ከሆነ በኋላ በአካ ባቢው ተደራጅተው የቆዩ አክራሪዎች፣ ሃርጂያ የሚባል አንድ የአክራሪዎች ድርጅትና ሌሎች መሰል የሙስሊም አክራሪዎች በዞኑ በአጠቃላይ ሙስሊሙ እያለቀ ነው በመሣሪያ እየታጨደ ነው፣ መስጊዶች ተቃጥለዋል እልቂት እየተፈጸመ ነው የሚል የውሸትና የማደናገር ወሬ በሰፊው ለማሠራጨት ችለዋል።

በወቅቱም በቅርቡ በገጠር አካባቢ የገባ ውን የቴሌፎን አገልግሎት ለዚሁ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ሰላም ዓላማ ተጠቅመውበት በአጭር ጊዜ ውስጥ ውዥንብሩን በብዙ ገጠሮች ለማዳረስ ችለዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ እነዚህ የተቀናጁ የሃርጂያና የሌሎች አክራሪ ቡድኖች በየገ ጠሩ ተቀናጅተው በሰፊው በመንቀሳቀስ ግድያዎችን ፈጽመዋል፤ ቤቶችን አቃጥለዋል፤ አልፎ አልፎ ቤተክርስቲያኖች አቃጥለዋል፣ አስገድዶ ሃይማኖት የማስቀየር ሥራን ሠርተዋል። ሁኔታው ከዳር እስከ ዳር በአጭር ጊዜ በተቀጣ ጠለበት ሁኔታ የአካባቢው ፖሊሶች ክስተቱን ለመቆጣጠር ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል።

ከዚህ ጋር በተያያዘ የክልሉ አስተዳደር ተጨማሪ ድጋፍ እንደሚያስፈልገው ስለጠየቀ ከመከላከያና ከፌዴራል ፖሊስም ተጨማሪ ኃይሎች ወደ ቦታው ተልከው ሁኔታውን ለማረጋጋት ችለዋል። በዚሁ ሒደት በርካታ ጉዳት ደርሷል፤ በድምሩ 19 ሰዎች ሞተዋል፤ ከእነዚህ ውስጥ 13ቱ የክርስትና እምነት ተከታዮች ሲሆኑ፤ 6ቱ ሙስሊሞች ናቸው። 37 ሰዎችም ቆስለዋል። ከእነዚህ ውስጥ 25ቱ የክርስትና እምነት ተከታይ ሲሆኑ አስሩ ሙስሊሞች ናቸው፤ ሁለት ፖሊሶችም በዚሁ ሒደት ቆስለዋል።

የተቃጠሉ ቤቶችን በተመለከተም ወደ 6 የሚጠጉ ቤቶች ተቃጥለዋል፤ 5 ያህል ቤተክርስቲያናት ተቃጥለዋል፤ 6ቱ የማቃጠል ወይም የማፍረስ ሙከራ ተደርጎባቸዋል፣ አንድ ቤተክርስቲያን የንዋየ ቅድሣት ንብረትና የንብረት ዘረፋ ተፈጽሞበታል። ስድስት የፕሮቴ ስታንት ሃይማኖት ቤተክርስቲያናት በወቅቱ ወደ መስጊድነት ተቀይረው ነበር።

ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በወቅቱ ሁኔ ታው በጣም ፈጣን በሆነ መልኩ በመቀጣ ጠሉ ምክንያት ለማስቆም ባይቻልም ወዲያውኑ የክልሉ መንግሥትና የፌዴራሉ መንግሥት በመተባበር በመጀመሪያ ደረጃ የተደረገው የወንጀሉ ጠንሳሾችና አንቀሳቃሾች፣ በወንጀሉ ተሳታፊ የነበሩና የወንጀሉ ተባባሪዎች በሦስት ደረጃ ከፍሎ መለየት ማጋለጥና በየደረጃው የእርምት እርምጃ መውሰድ ነበር።

የወንጀሉ ዋነኛ ጠንሳሾችና አንቀሳቃሾች ከፍተኛ ወንጀል በመፈጸማቸው ለፍርድ የሚቀርቡበት፣ በቤት ማቃጠልና በመሳሰሉት ተግባሮች የተሳተፉ ፈጻሚዎች በተመሳሳይ መልኩ ወደ ፍርድ እንዲቀርቡ የማድረግ፣ እነዚህን ወንጀሎች ባይፈጽሙም በወንጀሉ ተግባር ላይ ተባብረዋል ተብለው የሚገመቱ ሰዎችን ደግሞ ለአጭር ጊዜ በቁጥጥር ሥር በማዋል አስተምሮ የመልቀቅ ሥራ ለመሥራት ተሞክሯል። በዚህ ሒደት ሕዝቡን በመሰብሰብ የተፈጠረው ጉዳት ምን እንደሚመስል በማሳየትና በማስረዳት ሕዝቡ ለሰላም አብሮ እንዲንቀሳቀስ ሰፊ ሕዝብን የማሳመንና የማስረዳት ሥራ ተሠርቷል።

ሙስሊሙም ክርስቲያኑም በከፍተኛ መጠን ተፀፅቷል- አዝኗል፤ በመፀፀትና በማዘን ሳይገደብ ወንጀሉን ፈጽመዋል የሚላቸውን ሰዎች አንድ በአንድ ነቅሶ አውጥቷል።

በዚሁ መሠረት ከወንጀሉ ጠንሳሾች ጥቂቶቹ ቢያመልጡም የተቀሩት ግን ሙሉ በሙሉ በቁጥጥር ሥር ውለዋል። በዚህ እንቅስቃሴ ውስጥ ዋነኛ ተዋናይ የነበሩት አክራሪ ሙስሊሞች የአካባቢው ሰዎች እንዳ ልሆኑ ለማረጋገጥ ተችሏል፤ የጅማም ሆነ የኢሉ አባቦራ ዞኖች ተወላጅ አይደሉምም፤ ከሌሎች አካባቢዎች የመጡ እንደሆነና ይህንን የአክራሪነት ሥራ ለመሥራት የተሰማሩ ሰዎች እንደ ሆኑ ተረጋግጧል። በእርግጥ ከአካባቢው ተወላጆች አብረዋቸው የተሳተፉ እንዳሉም ይታወ ቃል። ከእነዚህ ሰዎች የተያዘው ተይዟል ያልተያዙ ጥቂቶችንም ፖሊስ ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ነው።

በተመሳሳይ መልኩ የወንጀሉ ዋነኛ ጠንሳሾችና ፈጻሚዎች ባይሆኑም በማቃጠል ወይም በሌላ ተግባር ላይ ተሰማርተዋል የሚባሉ ሰዎችም እንደዚሁ ኅብረተሰቡ አንድ በአንድ ነቅሶ አውጥቷቸዋል - አጋልጦአቸዋልም። በቁጥጥር ሥር እንዲውሉ ተደርጎ ለፍርድ እንዲቀርቡ እየተደረገ ነው። በሁለቱም ዞኖች በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ተጠርጣሪዎች ታስረው ለፍርድ ቀርበዋል።

ሌላው በስልክም በአካልም ሙስሊሙ እያለቀ ነው ተብሎ ያልሆነ ወሬ ተነግሮት ተደናግጦ የእነዚህ ሰዎች የወንጀል ተግባር ተባባሪ የሆነው የኅብረተሰብ ክፍልንም ሕዝቡ አጋልጦ አውጥቷል፤ ለተወሰኑ ቀናት በቁጥጥር ሥር ውሎ የፈጸመው የተባባሪነት ወንጀል ምን እንደሆነ እንዲረዳውና በሥራው ስህተት ተፀፅቶ ወደ ሰላማዊ ኑሮው እንዲመለስ እየተደረገ ነው ያለው። ከዚህ ጋር በተያያዘ ተቃጥለው የነበሩ ቤቶችን የአካባቢው ሕዝብ በደቦ በአብዛኛው ሠርቷል፤ ተፈናቅሎ የነበረውም ሰው በአብ ዛኛው ወደ ነበረበት ሁኔታ ተመልሷል። እንደዚሁም ተቃጥለው የነበሩ ቤተክርስቲያናት አብዛኛዎቹ ተሠርተው ሥራቸውን ጀምረዋል፤ አክራሪዎቹ ወደ መስጊድነት ቀይረዋቸው የነበሩ ቤተክርስቲያናትም የተለመደ የቤተክርስቲያን ግልጋሎታቸውን እንዲያከናውኑ ተደርጓል፤ በጉልበት ሃይማኖታቸውን እንዲቀይሩ ተገድ ደው የነበሩትም ወደ ፈለጉት ሃይማኖት እንዲ መለሱ እየተደረገ ነው።

ከጥቂቶቹ በስተቀር ብዙዎቹ የአካባቢው የሃይማኖት መሪዎች፣ ከሙስሊሙም ከክርስቲያኑም የተከሰተውን ችግር በመቋቋም ረገድ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውተዋል። ሕዝቡንም በማስረዳትና በማሳመን ኢትዮጵያ ከብዙ ሌሎች ሀገሮች በተለየ ሁኔታ በሙስሊምና በክርስትና እምነት ተከታዮች መሐከል የመቻቻል፣ አብሮ የመኖር ባህል እንዳለ ይህንንም ባህል ለማፍረስና ለማጥፋት የሚጥሩ ከሁለቱም ወገኖች አክራሪዎችና ፀረ-ሰላም ኃይሎች የራሳቸው የፖለቲካ አጀንዳ ያላቸው ወገኖች እንደሆኑ፣ ሕዝቡ የእነዚህ ሰዎች የተሣሣተ ቅስቀሳና የውሸት ወሬ ሰለባ መሆን እንደሌለበት በማስረዳት ችግሩን ለመቀነስ፣ ከተፈጸመም በኋላ ለማረጋጋት ሰፊ ሥራ ሰርተዋል፤ በዚህም ሊመሰገኑ ይገባል።

ይህ በእንዲህ እንዳለ ከክርስቲያኑም ከሙስሊሞቹም ጥቂቶች የሃይማኖት መሪዎች ነን የሚሉ ግለሰቦች ችግሩን በመፍጠርም ሆነ በማባባስ ረገድ የበኩላቸውን ድርሻ ተጫውተዋል፤ እነዚህ ቀደም ሲል እንደገለጽኩት በቁጥጥር ሥር ውለዋል።

በአሁኑ ሰዓት በአካባቢው አስተዳደር ሕዝቡን የማረጋጋትና ጉዳዩ እንደገና እንዳይደገም ከሚደረገው የማስረዳትና የማሳመን ሥራ ባሻገር ከአካባቢው የሃይማኖት መሪዎች የተውጣጣ ኮሚቴ ተደራጅቶ በየአካባቢው ተንቀ ሳቅሶ ሕዝቡን በማስተማርና በማስረዳት ላይ ይገኛል።

ሆኖም የተፈጠረውን ችግር በሕዝቦች መካከል ግጭትና ቅራኔ ለመፍጠር ሆን ብለው የሚጠቀሙበት ኃይሎች ከሁለቱ ዞኖች ውጪ በአዲስ አበባም በሌሎችም እንዳሉ ይታወቃል። በአዲስ አበባ በሲዲ እና በመሳሰሉት መልኩ የተቀረጹ ምስሎችን በመያዝ ቅስቀሳዎች በመደረግ ላይ ናቸው፤ አልፎ አልፎም በሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች በመስጊዶችም በቤተክ ርስያናትም ቅስቀሳ እየተካሄደ እንደሆነ ይታወ ቃል። እግረ መንገዴንም ልጠቅስ የምፈልገው በሁለቱም ዞኖች በገጠር አካባቢ ወሬው በአጭሩ ሊዛመት የቻለበት አንዱ ምክንያት የገባውን አዲስ የቴሌኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ የፀረ-ሰላም ኃይሎቹ በሰፊው ሊጠቀሙበት ስለቻሉ ነው። እዚህም አዲስ አበባ የተለያዩ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን እየተጠቀሙ የቅስቀ ሳውን ሥራ እያካሄዱት ነው ያሉት።

በዚህ ተግባር ላይ አሁንም አብዛኛዎቹ፣ እጅግ የሚበዙቱ የሃይማኖት መሪዎች የጅሃድና የመስቀል ጦርነትን አራማጆች እያወገዙ ሕዝቡ በሰላም ተደጋግፎና ተባብሮ እንዲኖር እያስተ ማሩ ያሉ ቢሆንም፤ ከሁለቱም ወገኖች ይሄንን ፀረ-ሰላም ተግባር ለማስፋፋት የሚንቀሳቀሱ የሃይማኖት መሪዎች እንዳሉ መንግሥት ለመገንዘብ ችሏል፣ በቅርብም እየተከታተለው ነው።

ፖሊስ በዚህ ፀረ-ሰላም ተግባር ላይ የሚሰማራ ማናቸውም ሰው በየትኛውም የኃላፊነት ደረጃ ይኑር፣ ምንም አይነት ካባ ይልበስ ወንጀል የፈጸመ በመሆኑ መንግሥት ተከታትሎ አስፈላጊና ሕጋዊ እርምጃ እንደሚ ወስድ ለምክር ቤቱ ለማረጋገጥ እፈልጋለሁ።

መንግሥት ከሚወስደው እርምጃ ይልቅ የላቀ ውጤት ይኖረዋል ብዬ የምገምተው ኅብረተሰቡ በራሱ የሚወስደው የመከላከል እርምጃ ነው። ቀደም ሲል እንደጠቀስኩት በኢትዮጵያ ውስጥ በእስልምናና በክርስትና ሃይማኖት መካከል መቻቻል የተጀመረው ዴሞክራሲን የመገንባት ጥረት እየተደረገ ባለበት በአሁኑ ጊዜ ብቻ ሳይሆን እስልምና ሃይማኖት ከተጀመረበት ወቅት ጀምሮ መቻቻሉ በሀገራችን የነበረ መሆኑ ይታወቃል።

የእሥልምና ሃይማኖት በተጀመረበት አካባቢ በሳዑዲ አረቢያ የነበሩት ዜጎች ይህንን በወቅቱ አዲስ የነበረውን ሃይማኖት ተከታዮች እያሳደዱ በሚገድሉበት ወቅት እነዚህ የመጀመሪያዎቹ የእሥልምና ሃይማኖት ተከታዮች ከሀገራቸው ተሰድደው የተጠለሉት ኢትዮጵያ ውስጥ ነው። ኢትዮጵያ ውስጥ ከመጡም በኋላ በወቅቱ የነበረው የክርስትና ሃይማኖት ተከታይ የሆነው አስተዳደር እነዚህን ሙስሊሞች ተንከባክቦ፣ ከጥቃት አድኖ በሀገራ ቸው ተመልሰው መኖር እሚችሉበት ደረጃ ላይ እስኪደርሱ ድረስ አስተናግዷቸዋል።

ስለዚህ የክርስትና ሃይማኖትና የእስልምና ሃይማኖት መቻቻል በሀገራችን

በየትኛውም ሀገር ይህ መቻቻል ከመጀመሩ በፊት የተጀመረ ነው። ረጅም ዕድሜ ያለው የመቻቻል ባህልም ነው።

ይህንን ባህል ለመበረዝና ለማጥፋት የሚንቀሳቀሱ አክራሪ ወገኖች አሉ። እነዚህ አክራሪዎች አንዱ ሌላውን እየመገበ ነው፤ ጂሃዲስቶች አንዳንድ አክራሪ ክርስቲያኖችን እየመገቡ ነው፡ እነዚህ አክራሪ ክርስቲያኖች ደግሞ ጂሃዲስቶችን እየመገቡ ነው። ሁለቱም ተመጋግበው የየራሳቸውን የፖለቲካ አጀንዳ ለማራመድ በሰላም የሚኖረውን ሕዝብ ለማጫረስ ጥረት እያደረጉ ነው። ይህንን ለመቋቋም የሚችለው ከመንግሥትም በላይ ሕዝቡ ነው። በዚህ ደረጃ በመስጊድም ሆነ በየቤተክርስቲያኑ የሚቀሰቅሱ የጥፋት መልዕክተኞችን ማስታገስ፣ ከማስታገስም አልፎ ለመንግሥት ተገቢውን መረጃ የመስጠት ኃላፊነትና ግዴታ ያለው ይመስለኛል። በዚህ ደረጃ የሚደረጉ ቅስቀሳዎች በተለይም በወጣቶች አካባቢ ነው ይህ ችግር ጎላ ብሎ የሚታየው፤ ወላጆች ልጆቻቸውን የመምከርና የማስተማር ሥራ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

ስለዚህም ችግሩን ከመቋቋም አኳያ መንግሥት የሚወስደው እርምጃ እንደተጠበቀ ሆኖ ኅብረተሰቡ የበኩሉን ድርሻ እንዲወጣ ማሳሰብ እፈልጋለሁ።

ሰይፈ ደርቤ

አዲስ ዘመን, ህዳር 17/1999 ዓ.ም